የደቀ መዝሙርነት መርሐዎች

የክርስትና ሕይወት መርሐዎች
የመሪዎች መመሪያ

የክርስቲያን ሥነ-ምግባሮች
ትምሕርት 3፥ የእግዚአብሔርን ቃል ማጥናት፡- ክፍል 2

መግቢያ

ይህ ትምሕርት ከደቀመዝሙርነት መርሐዎች የትምሕርት መድብሎች አንዱ አካል ሲሆን፣ ርዕሱም "የክርስቲያን ሥነ-ምግባሮች" ይባላል። ይህ ተከታታይ ትምሕርቶችን ያቀፈው ክፍል፣ የክርስቲያን ሕይወት ሥነ-ምግባሮችን ማለትም፡- ፀሎት፥ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፥ እንደዚሁም አእምሮአችንን ዘላለማዊ ነገሮች ላይ ማሳረፍን ጨምሮ ያስተዋዉቃል። ይህ አስደናቂና አስደሳች ይዘት ወይም ፅንሰ ሃሳብ፤ ለነባርና በሳል አማኞች መንፈሳዊ ሕይወት ጉልበትና ጥንካሬ መስጠት አለበት፤ እንዲሁም ደግሞ፥ አዳዲስ አማኞችን ወደ ጠለቀ እምነት ማራመድ፥ማፍጠን ይገባዋል። ይህ በአፈፃፀም ባሕርይዉ ተግባራዊ የሆነዉ ጠቃሚ የትምሕርት መርጃ (ማቴሪያል)፥ ለእግዚአብሔር የተሰጠ ሕይወት ወደፊት ሊቀበል ያለዉ ብዙ መንፈሳዊ ዋጋ ወይም ወረታዎች ላይ የበለጠ ትኩረት ያደርጋል።

የታለመለት ተደራሲ

ለእነዚህ ትምሕርቶች ታላሚ ተደራሲ (የታለመለት ተጠቃሚ) የሚሆኑት፡- አዲስ ክርስቲያኖች ሲሆኑ፤ በሌላ ወገን ደግሞ ነባር አማኞች ሆነው፣ የክርስትናን መሠረታዊ መርሆዎች በበለጠ ግንዛቤ ጨብጠዉ ወደ ከፍታ ለመድረስ ተሐድሶን የሚሹ፤ አልፎም እነዚህን ክርስቲያናዊ ምግባሮችና እምነቶችን ለማስተማር የሚዘጋጁ ክርስቲያኖች ናቸዉ። በተጨማሪ፥ ክርስቲያን አስተምህሮ ላይ ዝንባሌ ያላቸዉም፣ በዕለት ከዕለት ኑሮአቸዉ፣ ለእምነታቸዉ ተገቢ የሆኑ ምርጫዎችን በሚያደርጉባቸዉ ጊዜያት፣ ከእነዚህ ትምሕርቶች ጠቃሚ እሴቶችን ያገኛሉ።

የመሪዎች መመሪያ ዓላማ፡- መሪዎችና አስተማሪዎች ትምሕርቶችን ሲያዘጋጁ ለመርዳት ነው። እነዚህን ትምሕርቶችና ቢጋሮች ከሌሎች "የደቀመዝሙርነት መርሐዎች" ማቴሪያሎች ጋራ በጥምረት መጠቀም ይቻላል። በድረ-ገፃችን፡ www.DEamharic.org ይመልከቱ።

ሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በ 1954 ዓም ከታተመዉ የድሮዉ (KJV) ትርጉም ሲሆን፥ በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር ፈቃድ ተቀድቶ የታተመ ነዉ።

ሌሎች ሁሉም ይዘቶች የ © 2019 ትራንስ ዎርልድ ራዲዮ ካናዳ ነው። ይህንን ግብአት ለመጠቀም ዋጋ እስካልጠየቁ ድረስ እና ስለ ክርስቶስ አለምን መድረስን አላማዎ አድርገዉ እስከሰሩ ድረስ በፈለጉት አይነት መንገድ ሊጠቀሙበት ይችላሉ። ተጨማሪ የፍቃድ ዝርዝሮችን በ www.discipleshipessentials.org/licensing ይመልከቱ.

የክርስቲያን ሥነ-ምግባሮች
ትምሕርት 3፣ የእግዚአብሔርን ቃል ማጥናት፡- ክፍል 2

ዓላማ

የዚህ ትምሕርት ዓላማ፣ ተሳታፊዎች የእግዚአብሔርን ቃል ትርጓሜ ሰጥተዉ፣ በሕይወታቸዉ ለመተግበር፣ በብቃት መረዳት እንዲችሉ የሚረዳቸዉን፤ የመጽሐፍ ቅዱስ አጠናን ዘዴ ምርምር ለመቀጠል ነዉ።

የመሪዎች ማስታወሻ

ይህ ትምሕርት ኢንደክቲቭ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ዘዴን መመልከት ይቀጥላል። በዚህ ትምሕርት ዉስጥ፣ የኢንተርፕሪቴሽን እና፣ የአፕሊኬሽን ደረጃዎችን አተገባበር ትለማመዳለህ። ተሳታፊዎች የጥቅሱን አፈታት ለመደገፍ ሌሎች ጥቅሶችን እንዲጠቀሙ ማበረታታት አስፈላጊ ነዉ። መጽሐፍ ቅዱስ ዉስጥ የሰፈሩልን የቃሉ እዉነታዎች ሁልጊዜ በሌሎች ጥቅሶች ይደገፋሉ። በአንፃሩም፣ የተሳሳተ አተረጓጎም ወይም አፈታት (ኢንተርፕሪቴሽን) ወደ ሐሰተኛ እምነቶች ሊመራ ይችላል። ስለዚህም በምናጠናበት ጊዜ ሁሉ፣ እንዲያስተምረን እና እንዲመራን፣ መንፈስ ቅዱስ ላይ መደገፍ በጣም አስፈላጊ ነዉ። ለዚህ ትምሕርት ጥናት ስትዘገጃጅ፣ ምናልባት ተማሪዎችህ ወይም ተሳታፊዎችህ ሊያገኟቸዉ የሚችሉአቸዉን፤ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መርጃ መሣሪያዎችን ለማሰባሰብ መትጋት ጠቃሚ ነዉ። ከብዙ በጥቂቱ፡- መጽሐፍ ቅዱስ በኢንተርኔት (አንላይን ባይብል)፣ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፣ የቃላትና ርዕሶች ዝርዝር ወዘተ.. ብዙ ሰዎች ጠቃሚ ሆነዉ አግኝተዋቸዋል። ምርጫህ የሆኑትን ትርጉሞች፣ በራስህ ቋንቋ የተዘጋጁትን ማፈላለግ ጥናትህን ምቹ እንደሚያደርገዉ አትዘንጋ። ጥቆማ፡- በእንግሊዝኛ ቋንቋ ተዘጋጅተዉ ኢንተርኔት ዉስጥ ከተጫኑት የጥናት መርጃ ማቴሪያሎች እነዚህን ፈትሻቸዉ፡- www.biblegateway.com፣ www.biblestudytools.com፣ www.biblehub.com።

መግቢያ

ከሚቀጥሉት ጥያቄዎች መካከል፣ ሁለት ወይም ሶስት ጥያቄዎችን መርጠህ፣ የቡድኑን አባላት ጠይቃቸዉ።

- ❖ከባድ የሆነብህን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ትርጓሜ (ፍች) ለመረዳት ስትሞክር፣ የተሟላ ግንዛቤ ለማግኘት ምን ታደርጋለህ? የትኞቹስ የመረጃ ምንጮች ላይ ታተኩራለህ? የምታጠናዉን ክፍል የበለጠ እንዲያብራሩና ግልፅ እንዲያደርጉልህ፣ ሌሎች ጥቅሶችን እንዴት መጠቀም ትችላለህ?
- ❖አብዛኛዉን ጊዜ የትኛዉን ጥቅስ ለማጥናት ነዉ የላቀ ፍላጎት ያለህ? የትኛዉንስ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ነዉ አዘዉትረህ ለመመልከት የምትነሳሳዉ?
- ❖መጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ ወይም ፍች (ኢንተርፕሪቴሽን) የሚያስፈልገዉ ለምንድን ነዉ? መጽሐፍ ቅዱስ ጠንከር ያለ ሥራ ካልታከለበት፣ እንዲያዉ እንደዋዛ በአንድ እይታ የማይገባ፣ ለመረዳትም ቀላል እንዳይሆን አስተዋፅኦ ያደረጉት ምክንያቶች ምንድን ናቸዉ?
- ❖“ኢንተርፕሪቴሽን” እና፣ “አፕሊኬሽን” የሚባሉት ቃላት ትርጓሜ ምንድን ነዉ?

ጥናት በሚቀጥሉት ነጥቦች ላይ ለቡድኑ በቂ ትምሕርት ስጥ፡-

ትምሕርት

❖**የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል መፍታትን መማር፡-** የመጽሐፍ ቅዱስን ጥቅስ ከተመለከትን (ካነበብን) በኋላ፣ ቁልፍ የሆኑ ዝርዝሮቹን ለማስተዋል፤ ፍች ለመስጠት ዝግጁ ነን ማለት ነዉ። አንድን ዱኩሜንት ከአንድ ቋንቋ ወደ ሌላኛዉ ቋንቋ የሚፈታ ወይም የሚመልስ ሰዉ ሚና ተርጓሚ ይባላል። ይህ ሥራ፥ የሁለቱንም ቋንቋዎች ታላቅ እዉቀት የሚጠይቅ ቢሆንም፤ ቀጥተኛ ወይም ቃል ለቃል ትርጉም፣ ዉጤታማ የግንኙነት ወይም የመልእክት ማስተላለፊያ መንገድ አይደለም። ስለዚህ፥ ተርጓሚ የቃሎቹን ትርጓሜ በሚገባ መረዳትና፤ ጽሑፉ የሚለዉን ፍች ለታለመለት ተደራሲ ወይም አንባቢ ማስተላለፍ ይጠበቅበታል። የመጽሐፍ ቅዱስን ጥቅስ መተርጎም እና ፍችዉን ማብራራት፥ በእርግጥ ትርጓሜዉን በትክክል ማስተዋልና መጨበጥን ይጠይቃል።

➢**ፍች መስጠት ጥያቄዎች መጠየቅን ይፈልግብናል፡-**

○ይህ ጥቅስ እዚህ ክፍልና ሥፍራ መሆን ያስፈለገዉ ለምንድን ነዉ?

○ጸሐፊዉ በዚህ ጥቅስ ምን ለማለት ፈለገ?

○ይህ ጥቅስ፥ በቀደሙት ቁጥሮች ዉስጥ ከሰፈሩት ጥቅሶችና ክፍሎች፥ ብሎም ጥቅሱን ተከትለዉ ከሚመጡት ጥቅሶችና ክፍሎች ጋራ ተያያዥነት ያለዉ እንዴት ነዉ?

➢**ቁልፍ የሆኑ ቃላትን መለየት፡-** ይህ ምናልባትም በሚገባ የማታዉቃቸዉን ቃላት ትክክለኛ ትርጉም ለማግኘት፤ መዝገበ ቃላትን መጠቀም ያስፈልግህ ይሆናል።

➢**የምታጠናዉን ጥቅስ ለመፍታትና ለመገንዘብ እንዲረዱህ ሌሎች ጥቅሶችን በማመሳከር ተጠቀም፡-**

○በጥቅሱ አገባብ የቅርብ የሆኑት (በጥቅሱ ዙሪያ ቀድመዉና ተከትለዉ ያሉት ጥቅሶች) ምን ያመለክታሉ?

○ሰፋ ያለዉ ጽሑፍ አገባብ ምን ያመለክታል (መጽሐፉ፥ የመጽሐፉ ዓይነት ወዘተ..)?

○ማጣቀሻ መረጃዎች ማለትም፡- በመጽሐፍ ቅዱስ ዉስጥ ያሉና፥ ተዛማጅ ሃሳብ ያላቸዉ ማመሳከሪያ ጥቅሶች ምን ያመለክታሉ?

➢**ማስታወሻዎችን መያዝ፡-** ከጥቅሱ መልእክት ዉስጥ ተረድተህ የተቀበልካቸዉን፣ ሥነ-ምግባሮች ወይም፥ መሠረታዊ መርሆዎች ዝርዝር አስፍር።

➢**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ማቴሪያሎችንና ግብአቶችን ግኝት ማጣራት፡-** በኢንተርኔት ድረ-ገፆች ዉስጥ ብዙ የጥናት ማቴሪያሎች ወይም ልዩ ልዩ መረጃዎች አሉ። ተማሪዎችህ የሚያመሳክሩባቸዉን ተዛማጅ ድረ-ገፆችን፤ የአብያተ ክርስቲያናት ቤተ መጽሕፍትን፤ እንዲሁም ያለችግር መጠቀም የሚችሏቸዉን መርጃ መሣሪያዎች መጠቆም፥ ማመላከት ያስፈልጋል።

➢የደራሲዉን (የጸሐፊዉን) ፍላጎት እና መልእክት አጠቃልሎ በግልጽ ያሰፈረ፤ እጥር ምጥን ያለ መግለጫ ፃፍ።

❖በጎብረት ትርጉም (ፍች) መስጠት፦ አሁን ደግሞ፤ ከዚህ በቀደመዉ ትምሕርት ዉስጥ የተወያየንበትን ጥቅስ መለስ ብለን እንመልከት። ሮሜ 12:1-2 ን ከፍታችሁ አንብቡ። የሚቀጥሉትን ጥያቄዎች መጠቀም፣ እንዴት በሕብረት ትርጉሙን መግለጥ እንደሚቻል ያሳያል።

➢የእነዚህን ቃላት፦ አትምሰሉ፣ መታደስ፣ ርኅራኄ፣ ትርጉም እንዴት ታቀርባለህ?
ጳዉሎስ "ይህን ዓለም አትምሰሉ" እና "በልባችሁ መታደስ ተለወጡ" ሲል ምን ማለቱ ነዉ?

➢ከላይ በተጠቀሱት ቃላትና ሐረጎች ላይ ብርሃን የሚፈነጥቁ የተወሰኑ ጥቅሶችን ፈልገህ ተመልከት። መጀመሪያ በጥቅሱ አገባብ ዙሪያ የቅርብ የሆኑትን ጥቅሶች መሞከር፤ ቀጥሎም ተመሳሳይ ሐረጎችና፣ ጽንስ ሃሳቦችን ከሌሎች መጽሐፍትና ጥቅሶች ማፈላለግ ይመከራል።

○"ይህን ዓለም አትምሰሉ" ፦ 1ኛ ዮሐንስ 2:15-16፣

○"በልባችሁ መታደስ ተለወጡ" ፦ ቆላስይስ 3:1-4፣ ኤፌአሶን 4:22-24

➢ከጥቅሱ ነቅሰህ በማዉጣት የራስህ የምታደርጋቸዉ መርሆዎች (ፕሪንስፕልስ) ምንድን ናቸዉ?

○ሙሉ ለሙሉ እግዚአብሔር ላይ ማተኮር፤ ሁልጊዜም ድርጊቶቻችን ሁሉ እርሱን ደስ እንደሚያሰኙ ሆኖ መመላለስ ይጠበቅብናል።

○በዚህ ዓለም ዉስጥ በዙሪያችን ያሉት ሁሉ በሚያደርጓቸዉ ነገሮች መሳብና መወሰድ የለብንም።

○የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሁልጊዜ መፈፀም እንችል ዘንድ፤ አእምሮአችንን ያለማቋረጥ ማደስ ከምንም የላቀ ኃላፊነታችን ነዉ።

➢እንደ አስፈላጊነታቸዉ የሚገኙ ከሆነ፤ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላትን ማገላበጥ፣ ማስታወሻዎችን መፈተሽ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ሐተታዎች (ኮሜንታሪ) ቅኝት በብቃት ማንበብ ማጠቃለያዎችን ለማጠንከር ይረዳል።

➢የሮሜ 12:1-2 አጠር ያለ ማጠቃለያ ወይም መግለጫ ምን ሊመስል ይችላል?
የቅድስናን ሕይወት መኖራችን በእግዚአብሔር ፊት እንደ አምልኮ ይቆጠርልናል። ስለሆነም፣ ፊታችንን ከዓለም ላይ አንስተን ወደ እግዚአብሔር ስንመልስ፣ የበለጠ አጥርተን እንመለከተዉና፤ እርሱም ለሕይወታችን ያለዉን ዓላማ ጠንቅቀን እንረዳለን።

❖**አፕሊኬሽን፡-** በዚህ በአፕሊኬሽን ደረጃ፣ የጻፍናቸዉን መርሆዎችና፤ የአስተምህሮዉን ማጠቃለያ ወስደን በሕይወታችን የምንተገብርበት ሂደት ነዉ። እናም የሚቀጥሉትን ጥያቄዎች እንመልሳለን፡-

➢**ይህ 'እዉነት' በህይወቴ ዉስጥ ተግባራዊ የሚሆነዉ እንዴት ነዉ?**

➢**ከዚህ እዉነት የተነሳ፣ በሕይወቴ ዉስጥ ማድረግ የምወዳቸዉ ዉሱን ወይም የተለዩ ለዉጦች የትኞቹ ናቸዉ?**

➢**እነዚያን ለዉጦች ለማካሄድ የሚኖረኝ ዕቅድ ምንድን ነዉ?**

❖**መተግበርን (አፕሊኬሽን) መለማመድ፡-** ሮሜ 12:1-2 ጥቅስ እንደገና ተመልከት። በኢንተርፕሪቴሽን (ትርጓሜ) ደረጃ ለይተን የያዝናቸዉን መርሆዎች (ሥነ-ምግባሮች) በራሳችን ሕይወት ዉስጥ ተግባራዊ ማድረግ የምንችላቸዉ የትኞቹ ናቸዉ? የተወሰኑ ሃሳቦች ይህን ይመስላሉ፡-

- **ወደ ሃሳባቼ አትኩሬና አመዛዝኜ በመመልከት፥ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኙ መሆናቸዉን እርግጠኛ መሆን።**
- **ማንኛቸዉንም ድርጊቶቼን በመመርመር፣ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሚከናወኑ መሆናቸዉን ልብ ማለት ይገባኛል።**
- **ዕቅዶቼና ዉሳዎቼ ሁሉ በእግዚአብሔር ቃል እና በእርሱ ፈቃድ ላይ የተመሠረቱ መሆን ይገባቸዋል።**
- **በምላሳችን ዉስጥ ሞትና ሕይወት ስላሉ፣ የምናገራቸዉን ሁሉ በጥንቃቄ ማድረግ ይገባኛል።**

የዉይይት ጥያቄዎች

❖**ኢንደክቲቭ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ዘዴን ሞክረህ ታዉቃለህ? በእግዚአብሔር ሕግጋትና ፈቃድ ዉስጥ እንድትመላለስ የረዳህስ እንዴት ነዉ?**

❖**ጌታ መንፈስ ቅዱስ እና ፀሎት፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታችን ዉስጥ የሚጫወቱት ሚና ምንድን ነዉ?**

❖**በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ዉስጥ ኢንተርፕሪቴሽን እና አፕሊኬሽን አስፈላጊ የሆኑበት ምክንያት ምንድን ነዉ? የጥቅሱ ጽሑፍ የሚለዉን መልእክት ብቻ መገምገምና ማስተዋል (አፕሊኬሽን) ብቻ ለምን በቂ አይሆንም?**

❖**ኢንደክቲቭ የመጽሐፍ ቅዱስ አጠናን ዘዴን መረጃ ለማን ማካፈል ትችላለህ? በበኩልህ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድን መመሥረት፤ ካልሆነም ቀድሞ የተዋቀረ ቡድን ጋር የመቀላቀል ዕድል አለህ ወይ?**

ፀሎት

ጊዜዉን በፀሎት አጠናቅቀዉ። ስለ 'የእግዚአብሔር ቃል' ስጦታዉ እግዚአብሔርን አመስግኑት። ተሳታፊዎች ለእግዚአብሔር ቃል ጥናት ጊዜ እንዲለዩ እና፤ በእነዚህ ትምሕርቶች የቀሰሚቸዉን በሕይወታቸዉ እንዲገለገሉባቸዉ ፀልዩ። ሥራቸዉ ዉጤታማ እንዲሆን፤ ጥናታቸዉም የተለወጠን ልብ እና፣ ላቅ ባለ መሰጠት ማገልገልን እንዲያስከትልላቸዉ አፅንታችሁ ፀልዩ።